# ደህንነቱ በተጠበቀ መልኩ ማጽዳት እና COVID-19

## Safer Cleaning & COVID-19 Brochure – Amharic Translation

*August 2020*

### ደህንነቱ በተጠበቀ መልኩ ማጽዳት እና COVID-19

የበሽታ ስርጭትን ለመከላከል እንዲያግዝ ደህንነቱ በተጠበቀ መልኩ የማጽጃ ዘዴዎች እና ጀርሞችን መድሃኒት መርጫ መንገዶችን በተመለከተ እነዚህን ምክሮች ይከተሉ።

አጠቃላይ ጽዳት ማድረግ እና ከዛም መድሃኒት መርጨት እንደ COVID-19 ያሉ በሽታ አምጪ ተህዋስያንን ያስወግዳል። የአደገኛነት ደረጃቸው ዝቅተኛ የሆኑ የፅዳት እቃዎችን እና ዘዴዎችን በመጠቀም ጽዳት ማድረግ በቤትዎ ውስጥ ያለው እያንዳንዱ ሰው ደህንነቱ የተጠበቀ እንዲሆን ለማድረግ በጣም ጥሩ መንገድ ነው።

### የሚያስከትላቸውን አደጋዎች ይወቁ

ብዙ የጽዳት አቅርቦቶች እና የቤት ውስጥ ምርቶች ዓይንን ወይም ጉሮሮን የሚያስቆጡ፣ ራስ ምታት እና ሌሎች እንደ አስም ያሉ የጤና ችግሮች ሊያስከትሉ የሚችሉ ኬሚካሎች ይይዛሉ። ይህ የሆነበት ምክንያት በቆዳዎ ላይ እንደ በረኪና ያሉ የምርቶች ብናኝ በአፍና በአፍንጫ ወደ ውስጥ ከመሳብ ወይም ኬሚካሎችን በቆዳዎ በኩል ወደ ውስጥ በመግባቱ ምክንያት ነው። ደህንነቱ አስተማማኝ የሆነ የጽዳት ዘዴ ወይም ምርትን መጠቀም መጀመር እነዚህን የጤና አደጋዎች ለማስወገድ ይረዳል።

- አስም
- የቆዳ መቆጣት
- የዓይን መቆጣት
- ራስ ምታት

### መርዛማነታቸው ዝቅተኛ የሆኑ የጽዳት ምርቶችን ይጠቀሙ

በላያቸው ላይ **CAUTION (ጥንቃቄ)**፣ **WARNING (ማስጠንቀቂያ)**፣ **DANGER (አደገኛ)**፣ ወይም **POISON (መርዛማ)** የሚሉ ቃላት ያለባቸውን ምርቶች ያስወግዱ። እነዚህ ምርቶች ለጤንነትዎ ጎጂ የሆኑ መርዛማ ኬሚካሎችን ይይዛሉ።

**በምትኩ** EPA “Safer Choice (**ደህንነቱ የተጠበቀ ምርጫ**)” **ወይም** “Cradle to Cradle (**ክራድል ቱ ክራድል**)” **የሚል ምልክት ያላቸውን ምርቶች ይምረጡ።** እነዚህ ደህንነታቸው የተጠበቀ እና በኃላፊነት የሚደረጉ ምርቶች መርዛማነታቸው ዝቅተኛ ሲሆን ለጤናዎም ዝቅተኛ ስጋት የሚያስከትሉ ናቸው።

እንደ ቤኪንግ ሶዳ፣ ኮምጣጤ፣ የምግብ እቃዎች ሳሙና እና ውሃ ካሉ የተለመዱ ነገሮች የቤት ማጽጃዎችን ማዘጋጀት ይችላሉ። እነዚህን ነገሮች በማቀላቀል በቤትዎ ውስጥ ያሉትን አብዛኛዎቹን ነገሮች ለማፅዳት ሊያገለግሉ ይችላሉ።

ደህንነታቸው የተጠበቀ የማጽጃ መንገዶች አዘገጃጀትን ከ **Hazwastehelp.org** ላይ ይመልከቱ።

| **ደህንነታቸው የተጠበቀ የጽዳት መሳሪያዎችን ይጠቀሙ** |
| --- |
| አብዛኞቹን አካላት ለማፅዳት ከእነዚህ መሳሪያዎች ጋር ውሃ ወይም መርዛማነታቸው ዝቅተኛ የሆኑ የጽዳት ምርቶችን ይጠቀሙ።<br><br>• የጽዳት መሳሪያዎችን ያድርቁ<br>• ስፖንጅ<br>• መፈግፈጊያ ብሩሽ<br>• ማይክሮፋይበር ጨርቅ |
| **መድሃኒት ከመርጨትዎ በፊት ያጽዱ** |
| **ማጽዳት ይጀምሩ**<br><br>ማጽዳት ጀርሞችን፣ ቆሻሻን እና ዝቃጭ ነገሮችን ከተለያዩ አካላት ወይም እቃዎች ላይ ያስወግዳል። ቆሻሻን እና ጀርሞችን ከተለያዩ ነገሮች ላይ ለማስወገድ በሳሙና፣ መርዛማነታቸው ዝቅተኛ በሆኑ የጽዳት ምርትዎ፣ ውሃ፣ እና ፍትጊያ በመጠቀም ይጀምሩ። |
| **የመከላከያ አልባሳትን ይልበሱ**<br><br>ጓንት እና የተወሰነ የዓይን መከላከያን፣ የሚቻል ከሆነ የደህንነት መጠበቂያ መነጽርን በመጠቀም ቆዳዎን እና ዓይኖችዎን ለመጠበቅ አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎችን ይውሰዱ። ለራስዎ ንጹህ አየር ለመስጠት መስኮቶችን በመክፈት ሳንባዎን ከጉዳት ይከላከሉ። |
| **ካጸዱ በኋላ መድሃኒት ይርጩ**<br><br>የምርቱ የአጠቃቀም መመሪያ በሚገባ ተግባራዊ ከሆነ፣ መድሃኒት መርጨት ሁሉንም በሚባል ደረጃ ተላላፊ ጀርሞችን በኬሚካዊ መንገድ ያጠፋል። በቆሻሻ፣ በአፈር ወይም በአቧራ ላይ ምንም አይነት ተጽዕኖ የለውም። አንድን ነገር ካፀዱ በኋላ፣ ለዚያ ነገር ተስማሚ የሆነ በ EPA የተመዘገበ ማጽጃ መድሃኒትን ይጠቀሙ። ከዛም እነዛን ነገሮች በሚገባ ይጠራርጓቸው |
| **ደህንነቱ በተጠበቀ መንገድ ስለማጽዳት እና ቤተሰብዎን ከ COVID-19 ስለመጠበቅ የበለጠ ይገንዘቡ** |
| www.Hazwastehelp.org<br>www.kingcounty.gov/depts/health<br>www.shorelinewa.gov/covid<br>www.epa.gov/coronavirus |
| **ጥንቃቄ፣ ማስጠንቀቂያ፣ አደገኛ፣** ወይም **መርዛማ** የሚሉ ቃላት ያለባቸውን ምርቶች በሰሜን ሲያትል የቤት ውስጥ አደገኛ ቆሻሻ መሰብሰቢያ ቦታ ላይ በጥንቃቄ ያስወግዱ።<br><br>እሑድ፣ ሰኞ፣ ማክሰኞ ክፍት ነው: ከ 9:30 a.m. እስከ 4:30 p.m. |